# መመሪያ ቁጥር 1131/2018

# የዕቃዎች ስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ አሰጣጥ መመሪያ

# Directive No 1131/2026

# Advance Ruling on Rule of Origin Directive

ሚያዝያ፤ 2018 ዓ.ም/ May, 2026

አዲስ አበባ/ Addis Ababa

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.2

# መመሪያ ቁጥር 1131/2018

# Directive No. 1131/2026

## የዕቃዎች ስሪት አገር ቅድመ መረጃ አሰጣጥ መመሪያ

## Advance Ruling on Rule of Origin Directive

በአህጉራዊ ወይም አካባቢያዊ ወይም በሁለትዮሽ የቀረጥ ነጻ ንግድ ስምምነቶች፣ ወይም በአንድ ወገን የቀረጥ ነጻ ንግድ መደላድሎች አማካኝነት ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ማድረግ ለሚፈልጉ አምራቾች ለሚልኳቸው እቃዎች በስምምነቶቹ የተቀመጡትን የስሪት ሀገር መስፈርት የሚያሟሉ ስለመሆናቸው የኤክስፖርት ሂደት ከመጀመራቸው በፊት አስቀድሞ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ ትክክለኛ የሆነ የግብይት ውሳኔ እንዲወስኑ ለማስቻል በማስፈለጉ፤

በላኪው እና በኮሚሽኑ መካከል በስሪት ሀገር ሰርተፍኬት አሰጣጥ ላይ መተማመንን እንዲኖር በማድረግና ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን በስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ በኩል አስቀድሞ መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

እቃው በሚላክበት ወቅት የሚኖረውን የስሪት ሀገር የማረጋገጥ ሂደት በማስቀረት ቀልጣፋ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም ሂደት እንዲኖር ማስቻል በማስፈለጉ፤

የዕቃዎች የስሪት አገር አወሳሰን ቅድመ መረጃ አሰጣጥ ስርዓት በዓለም አቀፉ የንግድ ድርጅት (WTO) የንግድ ማሳለጥ ስምምነት አንቀጽ (3) መሰረት በማድረግ አሰራሩ በሀገራችንም እንዲተገበር በማድረግ የሀገራችንን የጉምሩክ አሰራር ዓለምአቀፍ

**WHEREAS**, it has become necessary to enable manufacturers and exporters, who intend to export their products through continental, regional, or bilateral free trade agreements, or unilateral duty-free trade arrangements, to obtain advance information regarding the fulfillment of rules of origin requirements prior to the commencement of the export process, thereby allowing them to make informed business decisions;

**WHEREAS**, it is essential to foster trust between the exporter and the Commission regarding the issuance of Certificates of Origin and to proactively resolve potential disputes through the provision of Advance Origin Rulings;

**WHEREAS**, it is deemed necessary to ensure an efficient customs procedure by eliminating the need for origin verification at the time of exportation, provided that an advance ruling has been issued;

**WHEREAS**, the system for Advance Rulings on Rules of Origin is recognized under Article (3) of the World Trade Organization (WTO) Trade Facilitation Agreement, and implementing this system in Ethiopia is vital to align the nation's customs operations with international standards;

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤ የገቢዎች ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 180/2/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**NOW, THEREFORE,** the Ministry of Revenues, in accordance with the authority vested in it by Article 180(2) of the Customs Proclamation No. 859/2006, hereby issues this Directive.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## Part One

## General Provisions

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የዕቃዎች ስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 1131/2018**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

1. **Short Title**

This Directive may be cited as the "**Advance Ruling on Origin Directive No. 1131/2026.**"

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፤

1/ **"የስሪት አገር ቅድመ መረጃ"፡-** ማለት ማንኛውም አምራች ወይም ላኪ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው የቀረጥ ነጻ ወይም ቀረጥ ቅናሽ ስምምነቶች ወይም የአንድ ወገን የንግድ ስምምነቶች ተጠቅሞ ዕቃውን ለመላክ ሲፈልግ፣ እቃውን የመላክ ሂደት ከመጀመሩ በፊት በስምምነቶቹ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ስለመሆኑ የስሪት አገር ቅድመ መረጃ እንዲሰጠው በእራሱ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ በኩል በኮሚሽኑ በተዘጋጀ

2. **Definitions**

In this Directive, unless the context requires otherwise:

1/ **"Advance Ruling on Origin "** means a written legally binding decision on the country of origin of a product provided by the commission to a manufacturer or exporter who seeks to export goods by utilizing the duty-free or reduced tariff schemes based on preferential trade agreements or unilateral trade agreement signed by Ethiopia; such request should be summited to the commission using the

ማመልከቻ አማካኝነት ጥያቄውን ሲያቀርብ፣ በጽሑፍ የሚሰጥ በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለው የስሪት አገር ውሳኔ ነው።

standard application form before the actual export of the goods directly by the exporter or manufacturer, or through a legal representative.

2/ **"የስሪት ሀገር የምስክር ወረቀት"** ማለት በቀረጥ ነጻ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ የተመረተ ምርት በስምምነቱ የተቀመጠውን መስፈርት ስለሚሟላቱ በኮሚሽኑ በኩል ሲረጋገጥ የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው።

2/ **"Certificate of Origin"** means a certification document issued by the Commission, upon verification, confirming that a product is originating in Ethiopia.

3/ **"ላኪ"ማለት** የቀረጥ ነጻ ወይም ቀረጥ ቅናሽ መደላድሎችን ተጠቅሞ እቃዉን ወደ ውጪ ሃገር የሚልክ ህጋዊ ሰው ወይም ድርጅት ነው።

3/ **"Exporter"** means a legal person or organization that exports goods outside the country by utilizing the duty-free or tariff preference agreements.

4/ **"ማመልከቻ ማቅረቢያ"**:- ማለት በኮሚሽኑ የሚዘጋጅ ሆኖ ላኪው የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ይሰጠኝ ጥያቄ የሚያቀርብበት ቅጽ ነው።

4/ **"Application Form"** means a form prepared by the Commission, which the exporter uses to submit a request for Advance Origin Ruling.

5/ **"ጥያቄ አቅራቢ"**:- ማለት የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ የሚያቀርብ ላኪ ወይም ህጋዊ ተወካይ ነው።

5/ **"Applicant"** means an exporter or a representative who submits a request for Advance Origin Ruling.

6/ **"የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ቅጸ" :-** ማለት በኮሚሽኑ ተዘጋጅቶ ለላኪው የስሪት አገር ቅድመ መረጃ የሚሰጥበት ቅጽ ነው።

6/ **"Advance Origin Ruling Form"** means a form prepared by the Commission and used to provide an Advance Ruling on Origin to the Exporter or manufacturer.

7/ **የቀረጥ ነጻ ስምምነት ፡-** ማለት ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችዉ እቃዎችን በቀረጥ ነጻ ወይም ቀረጥ ቅናሽ መላክ የሚቻለበት

7/ **"Free Trade Agreement"** means a regional, bilateral, or unilateral trade preference that Ethiopia has ratified to allow goods to be exported duty-free

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

የአህጉራዊ፣ አካባቢያዊ፣ የሁለትዮሽ፣ ወይም የአንድ ወገን የንግድ መደላድል ነው፡፡

or with at reduced duty rates.

8/ **ዳይሬክቶሬት፡-** ማለት በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ዋናው መ/ቤት የታሪፍ ምደባና ስሪት ሀገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

9/ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት፡-ማለት በኮሚሽኑ ዋና መ/ቤት የአቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

10/ **"ኮሚሽን"፡-** ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ነው፡፡

11/ **"አዋጅ"፡-** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ከነማሻሻያዎቹ ማለት ነው፡፡

12/ በዚህ መመሪያ ያልተካተቱ ቃላት እና ሀረጋት በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

8/ **"Directorate"** means Tariff Classification and Rules of Origin Directorate int the Head Office the Ethiopian Customs Commission.

9/ **"Appeal Review Office"** means the Appeal Review Directorate in of the Head Office of the Ethiopian Customs Commission.

10/ **"Commission"** means the Ethiopian Customs Commission.

11/ **"Proclamation"** means Customs Proclamation No. 859/2014 and its amendments.

12/ Words and phrases not defined in this Directive shall have the meanings assigned to them in the Proclamation.

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው የቀረጥ ነፃ የንግድ ስምምነቶችን ለመጠቀም ወደ ውጭ ሀገር በሚላኩ ዕቃዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3. **Scope of Application**

This Directive shall be applicable to all goods exported abroad utilizing the duty-free trade agreements ratified by Ethiopia.

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

## ክፍል ሁለት

## የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ አቀራረብ

4. የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ ሲቀርብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መረጃዎች እና ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡፡

   1/ የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው የቀረጥ ነጻ ስምምነትን ተጠቅሞ ምርቱን የሚልክ አምራች ወይም ላኪ ወይም ተወካይ ብቻ ነው፡፡

   2/ ጥያቄው የሚቀርበው በተወካይ ከሆነ ለተወካዩ የተሰጠ ህጋዊ የውክልና ሰነድ መቅረብ አለበት፡፡

   3/ የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ አቅራቢው በአባሪ "1" ላይ የተመለከተውን የጥያቄ ማቅረቢያ ማመልከቻ ቅጽ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ተጠቅሞ መረጃውን በአማርኛ ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ በትክክል ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

   4/ በአንድ የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ለአንድ እቃ ብቻ ነው፡፡

   5/ ጥያቄ አቅራቢው በጥያቄ ማቅረቢያ ማመልከቻ ቅጹ ላይ የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡-

## PART TWO

## APPLICATION PROCEDURES

4. **Requirements for Application**

   1/ A request for Advance Origin Ruling can only be submitted by a manufacturer, exporter, or representative who is exporting a product by utilizing a free trade agreement.

   2/ Where a representative submits the application, a valid and legally executed Power of Attorney must be provided.

   3/ Applications shall be submitted using the form prescribed in Annex-1, either in hard copy or electronically, in Amharic or English.

   4/ A request for Advance Ruling on Origin can only be submitted for one item at a time.

   5/ The applicant must specify the following in the application form:

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

ሀ) እቃውን ከቀረጥ ነጻ ወይም በቀረጥ ቅናሽ የሚልክበትን የቀረጥ ነጻ ስምምነት፤

ለ) እቃውን የሚልክበትን ሀገር፤

ሐ) የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ የሚቀርብበትን እቃ ሙሉ መግለጫ፤

መ) እቃውን ለመስራት ግብዓት የሆኑ የጥሬ እቃዎች ዝርዝር፤

ሠ) የጥሬ እቃዎቹ ዝርዝር መግለጫ እና ተጨማሪ መረጃዎች፤

ረ) እቃው የተሠራበት ግብዓት ምጥን ወይም የአሰራር ቀመር፤

ሰ) የእቃውን የአመራረት ሂደት፤

ሸ) የምርቱ እና የእያንዳንዱ ግብዓት (ጥሬ እቃ) የታሪፍ አመዳደብ ቁጥሮች፤

ቀ) ጥሬ እቃዎቹ የመጡበት ሀገር፤

በ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ "ቀ" የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ እና ከውጭ አገር ገብተው ጥቅም ላይ የዋሉት ለየብቻ ተለይተው መገለጽ አለባቸው፡፡

ተ) ለየግብዓቶቹ የወጡ ወጭዎች በዝርዝር መገለጽ አለበት፤

ቸ) ላኪው እንዲያሟላው የሚጠበቅበትን የዕቃዉን ልዩ የስሪት ሀገር መስፈርት መጠቀስ አለበት፤

a) the trade agreement under which the item will be exported duty-free or at a reduced rate;

b) the destination country of the item;

c) a full description of the item for which Advance Ruling on Origin is requested;

d) a list of input raw materials used to produce the item;

e) a detailed description of the raw materials and additional information;

f) the composition of the product or the production formula.

g/ the manufacturing process of the item;

h/ the tariff classification numbers of the product and each input (raw material);

i/ the country of origin of the raw materials

j/ Subject to the provisions of the letter "i" of this sub-section, those domestically sourced and imported goods must be listed separately);

k/ a detailed list of costs incurred for each inputs;

l/ Product specific Rule (origin criteria) that the exporter is expected to meet,

m/ Provided that the requirements

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.2

ኀ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሚሽኑ ሌሎች አስፈላጊ መስፍረቶችን እንዳስፈላጊነቱ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

set forth in this sub-article are met, the Commission may request other necessary measures as deemed necessary.

6/ ጥያቄ አቅራቢው ከጥያቄ ማቅረቢያው ቅጹ ጋር እንዳስፈላጊነቱ የምርቱን እና ጥሬ እቃዎችን ወይም ግብዓት ናሙናዎች፤ግብአቱን የሚመለከቱ ቴክኒካዊ ማብራሪያዎች እና እንደ ብሮሸር፣ ካታሎግ፣ ፎቶግራፍ፣ ቪዲዮ ያሉ ማስረጃዎች፤ እቃውን የተመለከቱ የላብራቶሪ ውጤቶች እና የመሳሰሉ ሌሎች ጥያቄ የቀረበበትን እቃ የስሪት ሀገር በትክክል ለመወሰን ሊረዱ የሚችሉ ሰነዶችን እና ማብራሪያዎችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

6/ The applicant shall submit, along with the application form, samples of the product and raw materials inputs, as necessary, technical explanations and evidence relating to the inputs like brochures, catalogues, photographs, video; laboratory results related to the item, and other documents and explanations that can assist in accurately determining the country of origin of the item for which the request is submitted.

7/ ጥያቄ አቅራቢው በቅድመ መረጃው ላይ በሚስጥር እንዲያዝለት የሚፈልጋቸውን ጉዳዮች በጥያቄ ማቅረቢያ ቅጹ ላይ ማመላከት አለበት፡፡

7/ The applicant shall indicate in the application form any matters they wish to be treated as confidential in the Advance Ruling.

8/ የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ አቅራቢው ማመልከቻውን ሲያቀርብ የታደሰ የኤክስፖርት ንግድ ፈቃድ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጅ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

8 When submitting the application, the applicant for Advance Ruling on Origin must also submit a copy of a renewed export-business license and Taxpayer Identification Number (TIN).

9/ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ

9/ The applicant for Advance Origin Ruling can only submit the

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

አቅራቢው ጥያቄውን ማቅረብ የሚችለው ዕቃውን የመላክ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ብቻ ነው።

request before initiating the export process of the goods.

## ክፍል ሶስት

## PART THREE

## የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ምርመራ እና ውሳኔ አሰጣጥ

## THE PROCEDURE FOR THE ISSUANCE OF ADVANCE RULING ON ORIGIN

### 5. የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ማመልከቻ ምርመራ

### 5. Verification of the Application Advance Ruling on Origin

1/ ኮሚሽኑ በአንቀጽ 4 በተቀመጠው አግባብ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ለተጠየቀበት እቃ የቀረበው ማመልከቻ የተሟላ መሆኑን ያጣራል።

2/ ኮሚሽኑ ከማመልከቻው ጋር የቀረበውን ማስረጃ መርምሮ የእቃውን የስሪት ሀገር ለመወሰን የሚረዳ ተጨማሪ ማስረጃ ካስፈለገው ከ10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለጥያቄ አቅራቢው በአድራሻው በተጻፈ ደብዳቤ ወይም በኤልክትሮኒክ መንገድ ይጠይቃል።

3/ ጥያቄ አቅራቢው ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ ከኮሚሽኑ ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ ከ10 የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማስረጃውን በደብዳቤ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ማቅረብ ይኖርበታል።

4/ ኮሚሽኑ ማስረጃው ሲሟላ ጥያቄ ለቀረበበት እቃ የሚላክበት የቀረጥ ነጻ ስምምነት ላይ የተቀመጠውን የስሪት ሀገር

1/ The Commission shall verify that the application submitted for an item requesting Advance Origin Ruling is complete, in accordance with the provisions of Article 4.

2/ The Commission shall request any additional Evidence necessary to determine the country of origin of the item from the applicant in writing, either by postal address or electronically, within 10 days of reviewing the submitted application

3/ The applicant, upon being requested by the Commission to provide additional Evidence, must submit the information in writing or electronically within a period not exceeding 10 working days from the date of the request.

4/ Once the Evidence is complete, the Commission shall determine whether

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

መስፈርት በመለየት በማመልከቻው ላይ ከቀረበው የምርቱ የአመራረት ሁኔታ እና ዝርዝር ማስረጃ ጋር በማነጻጸር የስሪት አገር መስፈርቱ ስለመሟላቱ ወይም ስለአለመሟላቱ ማጣራት ያደርጋል፡፡

the rule of origin criteria is met or not by identifying the rule of origin criteria stipulated in the duty-free agreement under which the item is to be exported and comparing those with the manufacturing circumstances and detailed information provided in the application.

5/ ኮሚሽኑ የቅድመ መረጃውን ለመስጠት የሰነድ ምርመራ በቂ እንዳልሆነ ካመነ ወይም የምርቱን አመራረት ሂደት ለማየት አካላዊ ፍተሻ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው አካላዊ ፍተሻውን ለማድረግ ቀጠሮ እንዲያዝለት ቀን ቆርጦ በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ለጥያቄ አቅራቢው ያሳውቃል፡፡

5/ When the Commission deems that a documentary investigation is insufficient to provide the Advance Ruling, or finds it necessary to conduct a physical inspection to observe the product's manufacturing process, it shall set a date for the physical inspection and notify the applicant in writing or electronically.

6/ ጥያቄ አቅራቢው በቀጠሮው ቀን የስሪት ሀገር ባለሙያው የሚፈልገውን ማስረጃ በማቅረብ እና የምርቱን የፋብሪካ ሂደት በማስጎብኘት እና ገለጻ በማድረግ መተባበር አለበት፡፡

6/ The applicant must cooperate by providing the information required by the origin verification expert on the scheduled date, facilitating a visit to the product's factory process, and providing explanations.

6. የስሪት አገር ቅድመ መረጃ አወሳሰን

6. Decision on of Advance Ruling on Origin

1/ ኮሚሽኑ ለቀረበው የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ አስፈላጊውን ጥናት ካደረገ በኂላ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ በአባሪ "2" መሠረት የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ቅጽ በመጠቀም ውሳኔውን ለጠያቂው እና ለሁሉም የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በደብዳቤ ወይም በኤልክትሮኒክ ዘዴ ያሳውቃል፡፡

1/ After conducting the necessary investigation for a submitted request to Advance Origin Ruling, the Commission shall notify its decision using the Advance Origin Ruling Form (Annex-2) or electronically to the applicant and all Customs Branch offices within 30 days from the date of accepting of complete application.

ኮሚሽኑ በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

2/ የቅድመ መረጃ ውሳኔ የሚያሳውቅበትን ጊዜ ለተጨማሪ 15 የስራ ቀናት ሊያራዝም ይችላል:-

ሀ) የማጣራት ሂደቱ ካለው ውስብስብነት አንፃር ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈለገው ከሆነ፤

ለ) ጥያቄ አቅራቢው የተጠየቀውን ተጨማሪ መረጃ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (3) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ ካልቻለ፤

ሐ) የላብራቶሪ ውጤት እና/ወይም የባለሙያ ማብራሪያ ማስረጃ በወቅቱ ካልደረሰ፤

3/ ጥያቄ አቅራቢው የተጠየቀውን ማስረጃ እንዲያቀርብ በተሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ማቅረብ ባይችልም ኮሚሽኑ አስቀድሞ በቀረበለት ማስረጃ ተመስርቶ ውሳኔ መስጠት የሚችልበት ሁኔታ ካለ ውሳኔውን ሊሰጥ ይችላል::

2/ The Commission may extend the period for notifying the issuance of Advance Ruling by an additional 15 working days for the following reasons፡

a) When the verification process requires additional time due to its complexity;

b) when the applicant fails to submit the requested additional information within the timeframe specified in Article5 (3);

c) When laboratory results and/or expert opinion information are not received in a timely manner.

3/ When the applicant fails to submit the requested information within the additional time granted, the Commission may still issue a decision based on the information previously submitted, provided it is sufficient to render a decision.

## 7. <u>የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ውሳኔ አሰጣጥና ውሳኔ ሰጪ አካል</u>

1/ ኮሚሽኑ የስሪት ሀገር መረጃ ሰርተፍኬት የመስጠት ስልጣን ይኖረዋል::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ እንደ አስፈላጊነቱ ሰርተፍኬት የመስጠት ተግባሩን ለቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች

## 7. Decision-Making Authority

1/ The Commission shall have the authority to issue an Advance Ruling on Country of Origin.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Commission or the Directorate may, as it deems necessary, delegate its power to issue rulings to the respective Customs Branch Offices.

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

በውክልና ሊሰጥ ይችላል::

3/ አምራቹ ወይም ላኪው እቃውን በቀረጥ ነጻ ስምምነት መሰረት ለመላክ የስሪት ሀገር ሰርተፍኬት እንዲሰጠው ሲጠይቅ ከኮሚሽኑ የተሰጠውን የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ኦርጅናል በደብዳቤ ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ አያይዞ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ለሚፈጸምበት ቅ/ጽ/ቤት ያቀርባል::

4/ ኮሚሽኑ ወይም የውክልና ስልጣን የተሰጠው ቅ/ጽ/ቤት የቀረበለትን የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ አይቶ በመረጃው የተጠቀሰው እቃ በቀረጥ ነጻ ስምምነት መሰረት ከሚላከው እቃ ጋር አንድ አይነት መሆኑን ሲያረጋግጥ ሰርተፍኬቱን ይሰጣል::

**8. <u>የውሳኔው ተፈጻሚነት</u>**

1/ አንድ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ የሚያገለግለው መረጃው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሦስት አመት ብቻ ነው::

2/ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ አስገዳጅ የሚሆነው በኮሚሽኑ ላይ ብቻ ነው::

3/ ኮሚሽኑ የሰጠውን የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ሌሎች አንድ አይነት እቃዎችን ለማስተናገድ በማጣቀሻነት ሊጠቀምበት ይችላል::

4/ ኮሚሽኑ ለአንድ ዕቃ የሰጠው የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ በስህተት የተሰጠ መሆኑን

3/ When the manufacturer or exporter requests a country-of-origin certificate for the purpose of exporting goods under a duty-free agreement, he shall submit the original country of origin advance information issued by the Commission to the customs office where the customs formalities are carried out, either by mail or electronically.

4/ The Commission or its authorized representative shall issue the certificate upon reviewing the preliminary information provided by the country of origin and verifying that the goods referred to in the information are identical to the goods to be exported under the duty-free agreement.

**8. Date of Validity**

1/ The advance origin ruling shall be valid for three (3) years from the date of issuance.

2/ The advance origin ruling shall be binding only on the Commission.

3/ The Commission may use the ruling as a reference for similar goods.

4/ The Commission may correct, revoke, or annul a ruling at any time if issued in error.

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

ሲያረጋግጥ በማንኛውም ጊዜ ስህተቱን ማረም እና ቅድመ መረጃውን መሻር ወይም መሰረዝ ይችላል፡፡

5/ ኮሚሽኑ ለአንድ ዕቃ የተሰጠን የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ በአንቀጽ 10 በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሲሽር ወይም ሲሰርዝ መረጃው የተሻረ ወይም የተሰረዘ ስለመሆኑ ከምክንያቱ ጋር ገልጾ ለአመልካቹ በደብዳቤ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ያሳውቃል፡፡

5/ When an issued advance ruling is revoked or annulled by the commission, the applicant shall be notified in writing or electronically with reasons thereof.

6/ ኮሚሽኑ አንድ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ የተሻረ ወይም የተሰረዘ ስለመሆኑ ለባለቤቱ ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ መረጃው አያገለግልም፡፡

6 A revoked or annulled ruling shall cease to have effect from the date of notification

7/ በንዑስ አንቀጽ (6) የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአንድ ዕቃ የተሰጠ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ከተሻረበት ወይም ከተሰረዘበት ቀን በፊት እቃውን የመላክ ሂደት የተጀመረ መሆኑ ከተረጋገጠ መረጃው ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

7/ Subject to the provisions of sub-article (6), if export procedures have already commenced before revocation or annulment, the ruling shall remain applicable to that export.

## 9. የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ሊሰጥ የማይችልባቸው ሁኔታዎች

## 9. Grounds for Non-Issuance The Commission shall refuse to issue a ruling

1/ ለዕቃው የስሪት አገር ለማረጋጥ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማግኘት ካልተቻለ፤

2/ የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ጥያቄ የቀረበበት ዕቃ ከአገር እንዳይወጣ በህግ የተከለከለ ከሆነ፤

1/ Where essential information required to determine origin cannot be obtained.

2/ where the goods to be exported are prohibited by law;

where the case is currently

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

9

3/ እቃው በኮሚሽኑ የአቤቱታ ሂደት ላይ የሚገኝ ከሆነ ወይም ከኮሚሽኑ ውጭ በፍርድ ቤት ወይም በነጻ ንግድ ስምምነት የግጭት አፈታት ሂደት ላይ ያለ ከሆነ፤

**10. የተሰጠ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ የሚሰረዝበት ወይም የሚሻርበት ሁኔታ**

1/ የተሰጠ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሻር ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) ቅድመ መረጃው በአመልካቹ በቀረበ የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ መረጃ ላይ የተመሰረተ ከሆነ፤

(ለ) ቅድመ መረጃው በኮሚሽኑ ስህተት የተሰጠ ከሆነ፤

(ሐ) በሀገራዊ ወይም በቀረጥ ነጻ ስምምነት ህጎች እና አሰራሮች መለወጥ ምክንያት ቅድመ መረጃው ጊዜው ያለፈበት ወይም የማይጣጣም ሆኖ ሲገኝ፤

(መ) ቅድመ መረጃው የተሰጠው ተገቢው ሥልጣን በሌለው ሰው ከሆነ፤

(ሠ) ቅድመ መረጃው የአገልግሎት ጊዜው የተጠናቀቀ ከሆነ፤

2/ ኮሚሽኑ በንዑስ አንቀጽ (1) በተገለጹት ምክንያቶች ቀድሞ የሰጠውን የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ሲሰርዝ ወይም ሲሽር ውሳኔውን ለቅድመ መረጃው ባለቤት

3/ under the Commission's complaint process, or is being handled outside of the Commission through a court of law or a Free Trade Agreement (FTA) dispute resolution process.

**10. Grounds for Annulment or Revocation**

1/ An Advance Ruling on Origin shall cease to have binding effect under any of the following circumstances:

(a) Where the ruling was issued based on incorrect or incomplete information submitted by the applicant;

(b) Where the ruling was issued due to an administrative or technical error committed by the Commission;

(c) Where the ruling becomes inconsistent with new or amended national legislation or provisions of a preferential trade agreement;

(d) Where the ruling was issued by an official acting beyond their delegated authority; or

(e) Upon the expiry of the validity period specified in this Directive.

2/ Where the Commission annuls or revokes an Advance Ruling pursuant to Sub-Article (1) of this Article, it shall immediately notify the holder of the ruling in writing or via the authorized electronic system, stating the specific

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

በጽሁፍ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

grounds for the decision.

## ክፍል

## ክፍል አራት

### 11. የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃ ውሳኔ ክለሳ እና አቤቱታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት

1/ ጥያቄ አቅራቢው የተሰጠው የስሪት አገር ቅድመ መረጃ ማሻሻያ እንዲደረግበት ቢፈልግ ምክንያቱን ገልጾ ውሳኔው በደረሰው በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ወይም ክለሳ እንዲደረግበት ለዳይሬክቶሬቱ በጽሁፍ መጠየቅ ይችላል፡፡

2/ ዳይሬክቶሬቱ ክለሳውን በ15 ቀናት አጠናቆ ውሳኔውን ያሳውቃል፡፡

3/ ጥያቄ አቅራቢው ባቀረበው የክለሳ ጥያቄ መሰረት ከዳይሬክቶሬቱ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው ውሳኔው በደረሰው በ15 የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለኮሚሽኑ የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4/ ጥያቄ አቅራቢው ከኮሚሽኑ አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው መደበኛውን የቅሬታ ሂደት ተከትሎ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

## PART FOUR

### 11. PROCEDURES FOR ADMINISTRATIVE REVIEW AND APPEAL

1/ Where an applicant seeks an amendment to an issued Advance Ruling on Origin, they may submit a written request for reconsideration or review to the Directorate within fifteen (15) working days from the date of receipt of the decision, stating the specific grounds for the request.

2/ The Directorate shall complete the review process and notify the applicant of its decision within fifteen (15) working days.

3/ An applicant dissatisfied with the review decision rendered by the Directorate may lodge an appeal to the Appeals Review Directorate of the Commission within fifteen (15) working days from the date of receipt of the review decision.

4/ Where the applicant remains dissatisfied with the decision issued by the Appeals Review Directorate of the Commission, they may pursue further recourse through the regular grievance procedures.

ኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሪከርድና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**12. መረጃን ስለማሳወቅ**

1/ ኮሚሽኑ የተሰጡ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክ ወይም አመች በሆነ ዘዴ አደራጅቶ ይይዛል፡፡

2/ ኮሚሽኑ የስሪት ሀገር ቅድመ መረጃውን ሌሎች አምራቾች እና ላኪዎች እንዲሁም የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲጠቀሙበት በኮሚሽኑ ድረ-ገፅ ወይም ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

3/ ኮሚሽኑ ጥያቄ አቅራቢው በሚስጥር እንዲያዝለት የጠቆማቸውን መረጃዎች ይፋ አያደርግም፡፡

**13. የስሪት ሀገር ለማረጋገጥ የምርመራ ወጭ**

ኮሚሽኑ የስሪት ሀገር ምርመራ ለሚያስፈልጋቸው እቃዎች ለሚወጡ የቤተ ሙከራ ምርመራ ወይም የባለሙያ አስተያየት ለሚያስፈልጋቸው ዕቃዎች የሚወጡ ወጭዎችን በጥያቄ አቅራቢው እንዲሸፈን ያደርጋል፡፡

## PART FIVE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**12. Disclosure of Information**

1/ The Commission shall organize and keep the issued advance ruling information on country of origin in electronic or other appropriate means.

2/ The Commission shall make the advance ruling on country of origin publicly available through the Commission's website or through an electronic system prepared for this purpose, so that other manufacturers, exporters, and all concerned parties may use it.

3/ The Commission shall not disclose information that the applicant has indicated should be kept confidential.

**13. Expenses for Country-of-Origin Investigation**

The Commission shall require the applicant to cover the costs incurred for laboratory testing or expert opinions necessary for goods that require country of origin investigation.

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

## 14. ወደ ውጭ ለሚላኩ ዕቃዎች የሚሰጥ የስሪት አገር ማረጋገጫን ስለ መተካት

በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠ አስገዳጅ የእቃዎች ስሪት አገር መረጃ እቃዎችን ወደ ዉጭ ለመላክ የሚሠጥን የስሪት አገር ማረጋገጫን ሊተካ አይችልም::

## 14. Non-Substitution of Export Proof of Origin

A Binding Origin Information issued in accordance with this directive cannot replace a proof of Origin issued for the export of goods

## 15. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገቢዎች ሚኒስቴር ድህረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

## 15. Effective Date of the Directive

This Directive shall enter into force as of the date of its registration with the Ministry of Justice and its publication on the official website of the Ministry of Revenues.

**አዲስ አበባ፣ ሚያዚያ 2018 ዓ.ም**

**አይናለም ንጉሴ አሊ**

**የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር**

**Addis Ababa, May, 2026 G.C.**

**Ayinalem Nigussie Ali**

**Minister, Ministry of Revenues**

ትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
Ministry of Revenues
Documentation No.2